# ሕገ መንግስታዊነት፣ ዴሞክራሲ
# እና
# የወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ እስር

ከስየ አብርሃ

(መጋቢት 20 ቀን 2001 ዓ.ም. የወ/ሪት ብርቱካን እስር ለማሰብ አዲስ አበባ በተጠራው ""‹ቃሌ› ሲምፖዝየም"" የቀረበ፡፡)

## መግቢያ

የአንድነት ለፍትህ እና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀ መንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ዳግም ከታሰረች ሦስት ወር ተቆጠረ፡፡ ዛሬ እዚህ የተገኘነው የእርሷን ዳግም መታሰርን ለማስታወስ፣ በዚህ አጋጣሚም የእሷ መታሰር በአገራችን ብዙ ስለሚነገርላቸው ሕገ መንግስታዊ ስርዓት፣ ሰብአዊ እና ዴሞክራሲ መብቶች ሁኔታ አንዳንድ የሃሳብ ልውውጥ ለማደረግ ነው፡፡

የወ/ሪት ብርቱካንን ዳግም መታሰር ሁሌም መታሰብ ያለበት ፖለቲካዊ ክስተት እንደመሆኑ የአንድነት ፓርቲ አባላት እና ደጋፊዎች ብቻ ሳይሆኑ በአገራችን ያለውን የሕገ መንግስት፣ የሰብአዊ እና የዴሞክራሲ መብቶች ጥሰት የሚቃወሙ  ኢትዮጵያውያን በመላ ሊያስቡት እና ሊያስታውሱት ይገባል፡፡ ይህን የምናደርገው በመጀመርያ ለራሳችን ስንል፣ ሁለተኛ ለእርሷ ብለን ሲሆን ሶስተኛ ደግሞ እንደ እርሷ ሁሉ መብታቸው ተገፎ እስር ቤት ለተቆለፈባቸው ሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ብለን ነው፡፡

በዚህች አገር ሕገ መንግስታዊነት ካልኖረ፣ በሕገ መንግስቱ የተደነገጉት ሰብአዊ እና ዴሞክራሲ መብቶች ካልተከበሩ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ከእስር ቤት ውጪ ያለነው ዜጎች እጣ ፈንታም የተለየ ይሆናል ብለን መጠበቅ አንችልም፡፡ በመብታችን መጠቀማችን ለጊዢዎቹ በስልጣን መቆየት አደጋ ነው በተባለበት ወቅት የእኛ እጣ ፈንታም ከወ/ሪት ብርቱኳን እና ሌሎቹ ታሳሪ ወገኖቻችን እጣ ፈንታ የተለየ አይሆንም፡፡ ይህንን አደጋ ልናስቀር የምንችለው በወ/ሪት ብርቱካን ላይ የተፈጸመውን የመብት ጥሰት በእያንዳንዳችን እንደተፈጸመ በመቁጠር ሁላችንም በያለንበት ሆነን በአንድ ድምጽ ስንቃወመው ብቻ ነው፡፡

ሕገ መንግስታዊ፣ ሰብአዊ እና ዴሞክራስያዊ መብቶቻቸው ተጥሶ እስር ቤት የተቆለፈባቸው በርካታ ወገኖቻችን አሉ፡፡ እነዚህም ከወ/ሪት ብርቱካን ጋር በእኩሌታ የሚታዩ ተበዳይ ወገኖቻችን ናቸው፡፡ በእህታችን ብርቱካን መብቶች መጣስ የበግነውን ያክል በእነዚህ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን መብት መጣስም መብገን ይኖርብናል፡፡ ወ/ሪት ብርቱካንን የምናስታውስበት እና የምናስብበት ስነ ስርዓት ሁሌም እነዚህን ድምጽ የሌላቸውን እና ሰማቸው እንኳ ዘርዝረን ልንጠቅሳቸው ያልተቻለን ድምጽ አልባ ወገኖቻችንን የምናስታውስበት ቀን መሆኑንም መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ወ/ሪት ብርቱካንን በስም እየጠራን የምናስታውሰው የእነዚህ ሰለባዎች ተምሳሌት በመሆንዋም ነው፡፡ በእሷ ስም በተጠራው በእንደዚህ አይነቱ ሰነ ስርዓት ሌሎች ሰለባ የሆኑ ወገኖቻችንንም ማስታወሳችን ስትሰማ ወ/ሪት ብርቱካን እንደምትደሰት ደግሞ እርግጠኛ ሆኜ መናገር እችላለሁ፡፡

ዳግም የታሰረችበትን ቀን ለማስታወስ በተዘጋጁት ስነ ስርዓቶች ስካፈል ዛሬ ሁለተኛየ መሆኑ ነው፤ ያለፈው በስነ ጽሁፍ እና ስነ ግጥም ነበር የታወሰው የዛሬው ደግሞ በሲምፖዝየም ነው፡፡ አቀራረቡ ድግግሞሽን ማስወገዱ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜም አዳዳዲስ እና ቁም ነገራቸው የላቀ ስልቶች እና መልእክቶች እየያዘ መምጣቱ የሚመሰገን መሆኑን፤ ወደፊትም በዚሁ አቅጣጫ እንድትሄዱ አዘጋጆቹን ምስጋናየንም ምክሬንም ለመስጠት እፈልጋለሁ፡፡

ለዚህ ሲምፖዝየም የሚሆን አንድ ጽሑፍ እንዳቀርብ ከአንድነት ስራ አስፈጻሚ ጥያቄ ሲቀርብልኝ ከዚህ በፊት ከእህታችን ብርቱካን ዳግም መታሰር በተያያዘ ያቀረብኩትን በመድገም ከማሰለቻችሁ ይልቅ ጉዳዩን ከሕገ መንግስታዊነት እና ከዴሞክራሲ አንፃር መዳሰሱን መርጫለሁ፡፡ ለዚህ መንደርደርያ ይሆን ዘንድ መጀመርያ ላይ ሰለ ሕገ መንግስታዊነት እና ሰለ ዴሞክራሲ ፅንሰ ሃሳብ የተወሰኑ  ነጥቦች አስቀምጣለሁ፡፡ ለወይዘሪት ብርቱካን ሁለቴ መታሰር ሰበብ የሆነው ምርጫ 97 እንደመሆኑ ምርጫ 97ን ሁሌ ከሚነገርለቱ ሕገ መንግስታዊነት እና ዴሞክራሲ ጋር በማያያዝ

የራሴን ግንዛቤ/ግምገማ አሳጥሬ አስቀምጣለሁ። መጨረሻ ላይ የወደፊት የተኩረት አቅጣጫ ላይ አስተያየቴን አስቀምጣለሁ።

## ሕገ መንግስታዊነትና ዴሞክራሲ

ሕገ መንግስት መንግስትን የሚያቋቁሙት ተቋማት ምንነት ይወስናል።መንግስትን የሚያቆሙት ተቋማት የስልጣን ማእከላት እንደመሆናቸው ሕገ መንግስት የእያንዳንዱን ተቋም ስልጣን ለይቶ ያስቀምጣል፤እያንዳንዱ ተቋም በተሰጠው ስልጣን ክልል የየራሱን ሥራ እየሰራ በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም ተቋማት በጋራ ሆነው አገርን እና ሕዝብን ያገለግሉ ዘንድ በመካከላቸው የሚኖረውን ግንኙነት ይደነግጋል። የሕገ መንግስት ዋና ተልእኮ የስልጣን ክፍፍልን መወሰን ነው የሚባለውም በዚሁ ምክንያት ነው❶።

የስልጣን ክፍፍል ማስጠበቅያ ሕግ እንደመሆኑ ሕገ መንግስት አንዱ የስልጣን ማእከል በሌሎቹ ላይ የበላይነት የሚያገኝበት ሁኔታን ያስወግዳል፣ እያንዳንዱ ነጻነቱ ተጠብቆ የሚሰራበት ሁኔታ መኖሩንም ያረጋገጣል። በተቋማቱ መካከል አንዱ ሌላውን የሚቆጣጠርበት ስርዓት እንዲኖር ማደረግ በአገሪቱ ማዛናዊ አስተዳደር ለመኖሩ ማረጋገጫ እና ዋስትና ነው።

ሕገ መንግስታዊነት (constitutionalism/constitutional liberalism) ከአጼዎቹ እና ከመሰል አገዛዞች የሚለይበት ትልቁ ቁም ነገር የታወቀ እና ተግባር ላይ የሚታይ የስልጣን ክፍፍል መኖሩ ነው። የተደነገገው የስልጣን ክፍፍል አጥጋቢ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል ዋናው ነገር የተደነገገ የስልጣን ክፍፍል መኖሩ እና ተግባር ላይ መዋሉ ነው። የአገሪቱ ርእሰ ብሄር ንጉሥ፣ ንግስት፣ ፕሬዚዳንት፣ አያቶላ ወዘተ ሊሆን ይችላል፤ ሕገ መንግስታዊ ለመባል ይበቃ ዘንድ ማለፍ ያለበት የመጀመርያው ፈተና በመንግስት ተቋማት መካከል የተደነገገ እና የሚሰራበት የስልጣን ክፍፍል መኖሩ ነው።

ሕገ መንግስታት የስልጣን ማእከላትን የስልጣን ክፍፍል ከመደንገግ አልፈው የዜጎች ሰብአዊ መብቶችን፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን፣ ስልጣን በምርጫ የሚያዝበትን ሁኔታ ሊደነግጉ ይችላሉ። ይህንን አሟልተው ሲገኙ ደግሞ ዴሞክራስያዊ ወይም ሪፓብሊካዊ የሚል ክብር እና መጠርያ ይጨመርላቸዋል። የስልጣን ክፍፍል መኖሩ እነዚህ መብቶች ለመከበራቸው ዋስትና ይሆናል። አንዱ የመንግስት አካል እነዚህን ባያከብር ሌሎቹ የመንግስት አካላት የገቺነት እና የአራሚነት ሚና በመጫወት እነዚህ መብቶች ሚዛን በጠበቀ መልኩ ጥበቃ እንዲያገኙ ያስችላል።

የተጠቀሱት መብቶች ይጠበቁ ዘንድ የስልጣን ክፍፍል ከመኖሩ በተጨማሪ ያገባኛል ባይ የኅብረተሰብ አካላት በሕገ መንግስቱ የተደነገጉትን መብቶች ተንተርሰው ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር የሚያስችሉዋቸውን መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ያቋቁማሉ። እነዚህ ተቋማት ለትርፍ የሚሰሩ የንግድ ተቋማት ሊሆኑ ይችላሉ፣ ለፖለቲካዊ ስልጣን የሚወዳደሩ የፖለቲካዊ ፓርቲዎች ሊሆኑ ይችላሉ፣የኅብረተሰቡን በጠቅላላ ወይም ደግሞ የተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች መብቶችን እና ጥቅሞችን ለማስጠበቅ የተቋቋሙ ሲቪክ ተቋማት ሊሆኑ ይችላሉ። የእነዚህ ተቋማት የጋራ ባህርይ ከመንግስታዊ ተቋማት ውጪ መሆናቸው ሆኖ ሕገ መንግስታዊው የስልጣን ክፍፍል ተግባራዊ በሚሆንበት ወቅት ከመንግስታዊ ተቋማቱ ጋር በጉድኝት ይሰራሉ፣ የስልጣን ክፍፍሉ በሚጣስበት ወቅት ደግሞ ኅብረተሰቡን ከጎናቸው በማሰለፍ የተፋለሰው ሕገ መንግስታዊነት ወደነበረበት እንዲመለስ ይታገላሉ።

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የተለያዩ ጥቅሞች ያሉዋቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የመኖራቸውን ያህል እነዚህን ጥቅሞች ለማስጠበቅ የሚቋቋሙት ተቋሞች የዝያን ያህል የተለያዩ ናቸው። መንግስት ሁሉንም ጥቅሞች በትክክል ያንጸባርቃል ተብሎ የማይገመተውን ያክል አንድ መንግስታዊ ያልሆነ ተቋምም የሁሉንም የኅብረተሰብ ጥቅም ያንጸባርቃል ተብሎ ስለማይጠበቅ የተለያዩ ተቋሞች በኅብረተሰቡ መኖራቸው አይቀሬ ነው።በአንድ አገር የበርካታ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ጠንካራ ተቋማት መኖር በአገሪቱ የዳበረ የስልጣን ክፍፍል እና የዳበረ ዴሞክራስያዊ ስርዓት ለመኖሩ ትልቅ መሰረት ነው።

ዴሞክራሲ ስልጣን ከህዝብ ይመነጫል ከሚል መርህ ይነሳል፤ በዚሁ መሰረትም አብልጫውን የሕዝብ ድምፅ ያገኘው ፓርቲ ስልጣኑን ይይዛል አገርንም ይመራል፡፡ አመራሩን የሚሰጠው ግን በሕገ መንግስቱ የተቀመጠውን የስልጣን ክፍፍል፣ ሕገ ምንግስቱ ያቋቋማቸውን መንግስታዊ እና መንግስዊ ያልሆኑትን ተቋማትን እና በሕገ መንግስቱ የተደነገጉትን መብቶችና ነፃነቶችን ጠብቆና አክብሮ እንዲሆን ይጠበቅበታል፡፡ የጨዋታ ሕጉ በሕገ መንግስቱ የተወሰነለት እና የተገደበለት በመሆኑ በዚያ መሰረት የመሄድ ግዴታ ይጣልበታል፡፡ ሕዝብ መርጦኛል፣ አብላጫ ድምፅ አለኝ በሚል የፈለግኩትን ላድርግ ቢል ግን ሕገ መንግስታዊነቱን ያጣል፡፡

አምባ ገነንነት ሊያቆጠቁጥ ከሚችልባቸው ሁኔታዎች አንዱ ዴሞክራሲን ከሕገ መንግስታዊነት ነጥሎ ማስኬድ ሲከሰት ነው፡፡ አንዳንድ መንግስታት በሕዝቡ በአብላጫ ድምፅ መመረጣቸውን ያሻቸውን ለማድረግ የሚያስችል ሰርቲፊኬት እንደተሰጣቸው አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ሕገ መንግስቱን እናከብራለን በሕገ መንግስቱ መሰረት እናስተዳድራለን እንዳላሉ ስልጣን ላይ ከተቆናጠጡ በኋላ የገቡትን ቃል መሃላ ገሸሽ ይላሉ፡፡ ሕገ መንግስታዊነትን ለመዋጋት ዴሞክራሲን እንደ ጦር መሳርያ መጠቀም ይታይባቸዋል፡፡ ዴሞክራሲን ከሕገ መንግስታዊነት ነጥሎ ማየት ከመጣ ደግሞ አንዳቸውም አይኖሩም፡፡ በቦታው የሚንሰራፋው አመባገነንነት ዝርፍያ እና ስርዓተ አልባነት ነው❷፡፡ በእንደዚህ ያለ ስርዓት ደግሞ ልማትም ሆነ ሰላም ህልም ሆነው ይቀራሉ፡፡ በብዙው መልኩ ከአዜዎቹ አገዛዝ የባሰ አገዛዝ ነው የሚፈጠረው፡፡

የድሮዎቹ የአዜዎቹ አገዛዞች የገቺነት ሚና ሊጫወት የሚችል የተደነገገ የስልጣን ክፍፍል ባይኖራቸውም በሕብረተ ሰቡ ውስጥ ለዘመናት የቆዩ ባህላዊ ተቋማት እና ልምዶች ትልቅ የገቺነት ሚና የሚጫወቱበት ሁኔታ ነበር፡፡ በእኛ አገር የአዜዎች አገዛዝ እንኳ ብንመለከት ንጉሠ ነገስቱ ውሳኔዎችን የሚወስነው ለዙፋኑ ቅርብ የሆኑ መኳንንትን ካማከረ በኋላ ነው፣ ፓትርያርኮችም የሃይማኖት መሪ ብቻ ሳይሆኑ አማካሪዎችም እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ መሪዎቹ ፈሪሃ እግዝአብሄርም የነበራቸው ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ግዝት እና ርግማን በመሪዎቹ ላይ ትልቅ የገቺነት ሚና እንደነበራቸውም ይታወቃል፡፡ እነዚህ ነባር ባህላዊ ተቋማት በአሁኑ ዘመን በሕብረተሰብ ያላቸው ስፍራ ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡ በአንዳንዶቹ አካባቢዎች ከጊዜው ሁኔታ ጋር እያደጉ እና እየበለጸጉ በመሄዳቸው አሁንም ትልቅ ስፍራ የያዙበት ሁኔታ ይታያል፡፡ በተለይ እንደ አፍሪካ ባሉ አካባቢዎች ደግሞ ወይ በኮሎንያሊዝም ተንኮታኩተው የተረሱበት ሁኔታ ላይ ናቸው ወይም ደግሞ ፈጣን በሆነ ሁኔታ ራሳቸውን ለዘመኑ የትርፍ እና የኪሳራ ሕግጋት በማስገዛታቸው የሞራል ልዕልናቸው እጅጉን የወረደበት ሁኔታ ላይ ናቸው፡፡

አንዳንድ የአፍሪካ መሁራን ሕገ መንግስታዊ ዴሞክራሲ (constitutional democracy) በአፍሪቃ ተጠናክሮ ያለመቆሙን በመመልከት እነዝያን ነባር ባህላዊ ተቋማትን እና ልምዶችን መልሶ በቦታቸው ማስቀመጥን እንድ አንድ የመፍትሄ አቅጣጫ ይጠቁማሉ❸ ፡፡ የዘመናችን ሰው ለመብቶች እና ለነፃነቶች ካለው ግንዛቤ ጋራ የሚሄዱ አገር በቀል እሴቶችን መጠበቁ እና መጠቀሙ ተገቢ ሆኖ፤ በስመ አገር በቀል ባህል እና ልምድ ከመሰረታዊ ሰብአዊ እና ዴሞክራሲ መብቶች ጋራ የሚጣረሱት ልምዶችን፤ ከተቆፈሩበት መልሶ ማምጣት ግን ለአምባገነኖች አፈና ተጨማሪ መሳርያ ከመሆን ያለፈ ፋይዳ አይኖራቸውም፡፡ ይህንን እውነታ ለመገንዘብ ሰሞኑ በተከሄደው የአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ የተሳተፉት የአፍረካ ባህላዊ ንጉሶች ንጉሰ ነገስት ያሉዋቸውን ሰው ይመለከቷል፡፡

አንዳንድ ተማራማሪዎች አውሮፓ ውሰጥ ከዴሞክራሲ በፊት ተግባር ላይ የዋለው ሕገ መንግስታዊነት ነው፣ አሁን ባሉት ያልዳበሩ አገራት ዘንድ ያለው የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ ያኔ አውሮፓ ውስጥ ከነበረው እድገት ብዙም ያልራቀ በመሆኑ እንደ አፍሪቃ ባሉት አካባቢዎች ስለዴሞክራሲ ከማወጋታችን በፊት ስለ ሕገ መንግስታዊነት ነው መነጋገር ያለብን ይላሉ❹፡፡ ይህን ሲሉ በሌላ አነጋገር፤ ባለንበት ዘመን፤ ያለ ዴሞክራሲ፤ ሕገ መንግስታዊነትን በቻ ይዞ ሰላምንና ልማትን ማምጣት ይቻላል እያሉ ነው፡፡ በእኔ እምነት ዴሞክራሲ በአለማችን ከአንድ ክፍለ ዘመን በላይ እድሜ ያስቆጠረ ስርዓት ነው፤ ካለንበት አለማዊ ትስስር አኳያ ዴሞክራሲ እና ሰብአዊ መብቶች ሁሉም የሚናገርባቸው የመላ የሰው ልጅ ተስፋዎች እሴቶች እንጂ ለተወሰነ የአለማችን ኅብረሰብ ግልጽ የሆኑለት ለሌላው ግን ምንም ትርጉም የማይሰጡ ሊባሉ የሚችሉ እሴቶች አይደሉም፡፡ ዴሞክራሲ እና ሰብአዊ መብት ሁሉም የሰው ልጅ የሚናገራቸው የጋራ ቋንቋዎች

በሆኑበት ሁኔታ ሕገ መንግስታዊነትን ከዴሞክራሲ ገንጥሎ ለብቻው ማስኬድ አይቻልም፡፡ ለዲሞክራሲ እና ለሰብአዊ መብት ጥበቃ የሚደረግ የተፋፋመ የሕዝብ ጥያቄ እና ትግል ባለበት ሁኔታ ይህንን እየዳመጡ ልማት እና ሰላም ብሎ ነገርም ሊታሰብ የማይቻል ነው፡፡

አፍሪቃውያን ከእንግዲህ ያላቸው አማራጭ ወደሙከራው መግባት እና በሂደት የጎደለውን ማሟላት እንጂ ዴሞክራሲን በይደር ማቆየት ወይም ጊዜ የተሻገራቸውን ባህላዊ ተቋሞች ከተቀበሩበት ማንሳት አይሆንም፡፡ አገር በቀል ከሆኑት በጎ ልምዶች እና ባህላዊ ተቋማት ሊወሰድ የሚገባውን መውሰድ ይገባል፤ የሌላው የአለም ክፍል ለምዶች ቢሆኑም ግን የመላ ሰው ልጅ እሴቶች ናቸውና ከሁሉም ሊወሰዱ የሚችሉትን በጎ እሴቶችን አጣምሮ እና ቀምሮ ከመሄድ ውጪ የሚቀርቡት ነጣጥሎ የማስኬድ አማራጮች የሚሰሩ አይመስለኝም፡፡ የአለሙ ማኅበረ ሰብም ማድረግ ያለበት አፍሪቃውያን ብቁ መሆናቸውን ተቀብሎ የጎደለውን እንደያሚሉ መርዳት እንጂ አንዱን ይዛችሁ ሌላውን ግን ገታ አድርጉ ማለት መሆን አይገባም፡፡ አይሰራምም፡፡

## ሕገ መንግስታዊነት እና አብዮታዊ ዴሞክራሲ

በአገራችን ኢትዮጵያ የሚቋቋም መንግስት ፌዴራላዊ፣ ዴሞክራስያዊም ሪፓብሊካዊም እንደሆነ በስራ ላይ ያለው የአገራችን ሕገ መንግስት ይደነግጋል፡፡ የፌደራል እና የክልል የሚባሉ ሁለት መንግስታት የያዘ ፌደራላዊ መንግስት እንደሚኖር ሲገልጽ ከዚሁ በተጨማሪ ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና ሕግ ተረጓሚ የሚባሉት ተቋማት ያሉት መንግስት በሁለቱም የመንግስት ስልጣናት እንደሚኖሩ ተደንግጓል፡፡ ሕገ መንግስቱ የጎድንዮሽ ላይ ብቻ ሳይሆን በተዋረድም የታወቀ የስልጣን ክፍፍል መኖሩን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

ሕገ መንግስቱ በግልጽ የተደነገገ ስልጣን ያላቸው በርካታ የስልጣን ማእከላት መኖራቸውን በመደንገጉ እንደአንድ ጥንካሬ ሊወሰድለት የሚችል ቢሆንም ይህንን ሕገ መንግስት ራሱን የመተርጎም ስራ ከፍርድ ቤት እጅ አውጥቶ ለፖለቲከኞች የሚተው በመሆኑ የስልጣን ክፍፍሉ ለአደጋ እንዲጋለጥ አድርጎታል፡፡ ይህንን ሕገ መንግስት የመተርጎም ኃላፊነት የተተወው ለፍዴሬሽን ምክር ቤት ነው፡፡ ሕግ ማውጣቱን ለፖለቲከኞች (ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት) መተዉ አግባብ ሆኖ በሚወጡት ሕጎችና በሕገ መንግስቱ መሃከል ተቃርኖ በማያጋጥመበት ጊዜ ፍቺው ለፖለቲከኞች (ለፌዴሬሽን ምክር ቤት) መተዉ በኤፌድሪ ሕገ መንግስት እንዲረጋገጥ የታሰበውን ሕገ መንግስታዊነት ይንዳል፡፡

ይህንን እውነታ ደግሞ ሰኔ 5 ቀን 1994 የወጣው የዋስ መብትን የሚከለክለው ሕግ አረጋግጦታል፡፡ ረቂቁ ጧት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ቀን ላይ ሕግ ሆኖ ለፍርድ ቤቶች እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ ሕጉ በሕገ መንግስት የተደነገገውን የዋስ መብትን የሚመለከተውን ድንጋጌ እንደሚጻረር ቢታወቅም ፖለቲከኞቹ ሕጉን ማውጣት አስፈላጊ ነው ብለው ስላመኑ በድምጽ ብልጫ አለፈ፣ ዳኞችም ሕገ መንግስት የመተርጎም ስልጣን የፍርድ ቤት አይደለም በማለት ተግባራዊ አደረጉት፡፡ የሚመለከተን ዜጎች ጉዳዩን ለሕገ መንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ብናቀርበውም ሕገ መንግስቱ አልተጣሰም ብሎ ጉዳዩን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዳይቀርብ አድርጓል፡፡ ይህ ሆኖም ሕጉ ሚያዝያ 97 በወጣ ሌላ ሕግ ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ሰኔ 93 ላይ ሕጉ እንዲጸድቅ ያደረጉት እና ከሕገ መንግስቱ ጋር ተቃርኖ የለውም ያሉት ፖለቲከኞች ሚያዝያ 97 ላይ ሕጉን ከሕገ መንግስቱ ጋር ማጣጣም ለማስተካከያው አንድ ምክንያት እንደሆነ ሲያብራሩ ተደምጠዋል፡፡ ይህ ምሳሌ ሕገ መንግስታዊነት በሌለበት ሁኔታ ሕግ ፖለቲከኞች እንደፈለጉ የሚያወጡት እና የሚቀይሩት የፖለቲከኞች ጦር መሳርያ እንደሚሆን ያመለክታል፡፡ ሕጉ በሕግ አውጪው አካል በድምጽ ብልጫ ያለፈ በመሆኑ ዴሞክራስያዊ ነው ሊባል ይቻል ይሆናል ሕገ መንግስታዊ ላለመሆኑ ግን ፖለቲከኞቹ ራሳቸው የሰጡት ምስክርነት በቂ ማረጋገጫ ነው፡፡

የኤፌድሪ ሕገ መንግስት ፌዴራላዊ የመንግስት አቋም አንደሚኖር ቢደነግግም በሕገ መንግስቱ የተደነገገው የተዋረድ የስልጣን ክፍፍል በተግባር እንደሌለ በክልሎች ያለው ሁኔታ አንድ ማሳያ ነው፡፡ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር የሚመራበት የአሰራር መርሕ ሌኒናዊ ዴሞክራሲያዊ ማአከልነት ነው፡፡ ኢህአዴግ በፌዴራሊዝም እና በዴሞክራሲያዊ ማእከልነት መርሆች መሃከል ያለውን ተቃርኖ የሚፈታው የፓርቲውን መርሕ በማስቀደም ስለሆነ እስካሁን ድረስ

በክልሎች የታዩት ሹም ሽሮች እንደሚያሳዩት የክልል ስልጣናት የሚኖሩት በሕገ መንግስቱ ሕልውና ሳይሆን በኢህአዴግ ፈቃድ ነው። በ1993 ዓ.ም በኢህአዴግ አመራር ውስጥ መከፋፈል መከሰቱን ተከትሎ አቶ ገብሩ አስራት፣ አቶ አባተ ኪሾ እና አቶ ኩማ ደመቅሳ ከክልል ፕረዚዳንትነት ስልጣናቸው የተነሱበት ሁኔታን ያስታውሷል። ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ወዲህ በሶማልያ ክልል ከአስር በላይ የክልል ፕረዚዳንት ሹም ሽሮች እንደተካሄደ ከሚያውቅ ሰው ሰምቻለሁ። ይህ ሁሉ የሆነው ክልሎቹ ስላስፈለጋቸው ሳይሆን ኢህአዴግ እንዲሆነ ስለፈለገ ነው።

የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሌኒናዊ የመንግስት እና የፓርቲ ፅንሰ ሃሳብ ነው የሚመራው። በመድብለ ፓርትያዊ ስርዓት ፈንታ የአንድ ፓርቲ ፍፁም የበላይነት ላይ ነው የሚቆመው፤ መንግስት ወጥ ነው ሆኖ የሚቆመው፤ የስልጣን ክፍፍል፤ ውስጣዊ ነፃነት፣ የተቋማት ገለልተኝነት ወዘተ  የሚባል ነገር የለም። በኢኮኖሚ ላይ ስለ ነጻ ገበያ፤ ስለ የግል ባለሃብት ድርሻ ብዙ ቢለፍፍም በስመ ‹‹ልማታዊ መንግስት›› መንግስት በኢኮኖሚ ላይ ያለውን ፍጹም የበላይነት አስጠብቆ ለመሄድ ይፈልጋል። ባለሃብቱን ‹‹ኪራይ ሰብሳቢ›› ብሎ ይፈርጀው እና በዚሁ ፈንታ የእሱ ፖለቲካዊ መሰረት ሊሆን የሚችል ሌላ ‹‹ልማታዊ ባለሃብት›› ይፈጠር ዘንድ የሃገር ሃብት እያፈሰሰ ይገኛል። ችግሩ እነዚህ ‹‹አልሚ›› ‹‹ተሸላሚ›› የተባሉት ‹‹ባለሃብቶች›› ብዙም ሳይቆዩ በራሱ በመንግስት ምስክርነት ‹‹አጥፊ›› ሆነው መገኘታቸው ነው። የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እና የኤፌድሪ ሕገ መንግስት ለየቅል መሆናቸው ይበልጥ ግልጽ ያደረገው ደግሞ ምርጫ 97 ነው።

## ምርጫ 97 እና የእነ ወይዘሪት ብርቱካን እስር

ኢህአዴግ ምርጫ 97 እንከን የለሽ ምርጫ ይሆናል ብሎ ቃል መግባቱ ይታወሳል።ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ወደ ውድድር የተጋበዙበትም ሆነ ክርክሩ የተጀመረበት መንፈስ ይህንኑ የሚያሳይ ነበር ማለት ይቻላል። ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የመንግስት መገናኛ ብዙኃን ለተቃዋሚዎችም ክፍት እንዲሆኑ ተደርጓል፤ ኢህአዴግና ተቃዋሚዎች በተመረጡ አጀንዳዎች ዙርያ አሉን የሚሉዋቸውን አቋሞችና ፖሊሲዎች ለሕዝብ አቅርበዋል፤ ተከራክረዋልም። በክልሎች ተንቀሳቅሰው አባሎችን ለመመልመልም ሆነ ሕዝቡን ለመቀስቀስ የሚችሉበት ሁኔታም ተፈጥሮ በዚሁም ቀላል የማይባል ስራ ሰርተዋል ማለት ይቻላል።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች መድረኩን አግኝተው ከኢህአዴግ ለመከራከር የገቡት ኃሳብን እና አቋምን የመግለጽ ነጻነት ሕገ መንግስታዊ ጥበቃ ያለው መብት ነው ከሚል እና በዚህ ጉዳይ እነሱም ሆነ ኢህአዴግ እኩል ነጻነት እንዳላቸው በማመን ነው። በምንም መልኩ የተናገሩት ወንጀል ነው ተብሎ ኂላ  አነሱን መክሰሻ ማስረጃ ይሆናል ብለው አልገመቱም።

በፉክክሩ እና በክርክሩ ሂደት በሕዝቡ ዘንድ የታየው አጠቃላይ ፖለቲካዊ    መነቃቃት እና ሕዝቡ ለተቃዋሚዎች እያሳየ የመጣው ድጋፍ ኢህአዴግ ያልጠበቀው በመኖሩ እያሳሰበው መመጣቱን የሚያመለክቱ ነገሮች ቢታዩም የግንቦት ስባቱ ምርጫም ቢሆን ሰላማዊ ሊባል በሚችል መልኩ ነበር የተካሄደው። ችግር የመጣው ምርጫው ከተከናወነ በኂላ ሲሆን ዋና ዋናዎቹን እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል።

### ሀ) የጠቅላይ ሚኒስትሩ ድንጋጌ

የምርጫው ዕለት ማታ በአዲስ አበባ ማንኛውም ሰላማዊ ሰልፍ እና የቤት ውጪ ስብሰባ በጠቅላይ ሚኒስትሩ መከልከሉን፣ ይህንን በማያከብሩ ላይ እርምጃ ለመወሰድ የሚችል ከመከላከያ፣ ከፌዴራል ፖሊስና ከአዲስ አበባ ፖሊስ  የተውጣጣ ጥምር ሃይለ መዘጋጀቱን እና ይህንን ሃይል የሚያስተባብር በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ እዝ መቋቋሙን በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬድዮ አማካኝነት ይፋ ሆነ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሃገሪቱ በመላም ሆነ በከፊል በሕገ መንግስቱ የተደነገጉትን መሰረታዊ መብቶችን ነጻነቶችን በከፊልም ሆን በሙሉ ለመገደብ የሚችልበት በሕገ መንግስት የተደነገገ ስልጣን የሌለው በመሆኑ የጠቅላይ ሚኒስትሩ እርምጃ ኢሕገ መንግስታዊ ለመሆኑ አንድ እና ሁለት የለውም። ቅንጅነት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ ይህንን የሕገ መንግስተ ጥሰት በመቃወም ፍርድ ቤት ዘንድ ክስ ቢመስርትም ዳኝነት ሊያገኝ አልቻለም።

ኢህአዴግ ይህን እርምጃ የወሰደው ውጤቱ ባልታወጀ ምርጫ ሂደት መሃከል፣ ፓርቲው ራሱ በስልጣን የመቀጠል ወይም ስልጣኑን የማጣቱ ጥያቄ በእንጥልጥል ባለበት ሁኔታ በመሆኑ፣ ስልጣን በሕዝብ ምርጫ ይያዛል የሚለውን ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ የማሰናከል ሚና ሊጫወት የሚችል ፀረ ዴሞክራቲክ እርምጃ መሆኑም የሚያከራክር አይደለም።

**ለ) እስር እና ደም መፍሰሱ**

ከግንቦት ሰባቱ ድንጋጌ ጀምሮ ኢህአዴግ የወሰዳቸው ተከታታይ እርምጃዎች ሲታዩ ምርጫው ሳይካሄድ በፊት የነበሩትን ሁኔታዎች ገምግሞ የወሰዳቸው እና አስቀድሞ የታሰበባቸው እርምጃዎች ናቸው የሚመስሉት።

በአንጻሩ ተቃዋሚዎች በ‹‹ይሆናል›› (what if?/Scenario) የተሰሩ አስቀድሞ የታሰበባቸው የስልት አማራጮች እና ይህን ለማስፈፀም የሚችል አመራርና ጠንካራ መዋቅር የነበራቸው አይመስልም። ኋላ ላይ በሕብረት እና በቅንጅት መካከል የተወሰነ ትብብር ቢታይም፣ በሁኔታ አስገዳጅነት የተፈጠረ እንጂ አስቀድሞ የታሸ እና የተሰራ ትብብር እንዳልነበረ ይታወቃል። የቅንጅቱ ጥምረትም ቢሆን ከጥምረት ወደ ውህደት ይሸጋገራል ተብሎ በመዋለል ሁኔታ ላይ እያለ፣ የጥምረቱ ሊቀ መንበር በገጠማቸው የጤና መታወክ ምክንያት ከኢትዮጵያ ውጪ በነበሩበት፣ ሌሎቹ ደግሞ አገር ውስጥ ባሉበት ሁኔታ ነው ፈጣን የሁኔታዎች መለዋወጥ የታየው።

ኢህአዴግ ቀደምትነቱን ወስዶ አስቀድሞ ያሰበባቸውን እርምጃዎች ተግባራዊ ማድረግ ሲጀምር፣ ተቃዋሚዎች ግን የራሳቸው ስልቶች ይዘው ሊወጡ ቀርቶ ለኢህአዴግ እርምጃዎች እንኳን ምን መልስ እንደሚሰጡ ተቸግረው አብዛኛውን ጊዜአቸውን በውይይት እና በስብሰባ የሚያጠፉበት፣ ሕዝቡ ምን እንደሚደረግ መንገድ የሚያሳይ አጥቶ መደናገር ውስጥ የገባበት ሁኔታ ነበር የተፈጠረው።

የብዙ ዜጎች ህይወት መጥፋት እና መቁሰል፣ የቅንጅት መሪዎችን ጨምሮ የበርካታ ዜጎች ለእስር መዳረግ የተከሰተውም በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው።

**ሐ) አጣሪ ኮሚሽን መቋቋሙ**

ደም መፋሰሱን ተከትሎ አጣሪ ኮሚሽን በአዋጅ መቋቋሙ ይታወሳል። ኢህአዴግ የኮሚሽኑ ተልእኮ ጥፋተኛ ማነው የሚለውን መለየት እንዳይጨምር አድርጓል። በዚሁ ፈንታ የኮሚሽኑ ተልእኮ ተብለው በማቋቋምያ አዋጁ የተቀመጡት የደረሰውን ጥፋት በዓይነት እና በመጠን ማጣራት፣ ‹‹መንግስት የወሰደው የሃይል እርምጃ ከመጠን ያለፈ ነበር? ወይስ አይደለም?›› ለሚለው የራሱን ሚዛን እና ግምገማ ማስቀመጥ የሚሉ ነበሩ።

የኮሚሽኑ ውሳኔ እና ኮሚሽኑ ራሱ መጨረሻ ላይ ምን ፈተና ውስጥ እንደገባ ይታወቃል። ኮሚሽኑ መጀመርያዉኑ ሲቋቋም ሊቀ መንበር እና ምክትል ሊቀመንበር እንዲሆኑ የተሾሙት ሁለት ዳኞች እና ከካቶሊካዊት ቤተ ክርስትያን ተወክለው በአባልነት የተመደቡት ዜጎች ባሉበት ኮሚሽኑ የወሰደው አቋም ‹‹መንግስት የወሰደው የሃይል እርምጃ ከመጠን ያለፈ ነው›› የሚል ሲሆን፣ ይህንን አቋም ለማስለወጥ በመንግስት የደረሰባቸው ጫና መቋቋማቸውን ተከትሎ ስጋት ሰላደረባቸው የተጠቀሱት ሶስት የኮሚሽኑ አባላት አገራቸውን እንደለቀቁ፣ ከዚህ በኂላ የተቀሩት የኮሚሽኑ አባላት ከመሃከላቸው ተተኪ ሊቀ መንበር እና መክትል ሊቀ መንበር እንዲኖራቸው እንደተደረገ እና ይህን ተከትሎም የተቀሩት የኮሚሽኑ አባላት መጀመርያ የተወሰደውን አቋም ቀይረው ሪፖርቱን ለፓርላማ ማቅረባቸው ይታወቃል።

በሁለቱም ሪፖርቶች ላይ ለብዙ ዜጎች መሞት፣ መቁሰል እና መታሰር ምክንያት የሆነው በመንግስት የጸጥታ ሃይሎች የተወሰደው የሃይል እርምጃ ለመሆኑ ለጥያቄ የሚቀርብ እውነታ አልነበረም፣ ልዩነት የታየው ይህ በመንግስት የተወሰደው እርምጃ ከመጠን ያለፈ ነው ወይስ አይደለም እሚለው ላይ እና በዚሁ ብቻ እንደነበረ ልብ ሊባል ይገባል።

**መ) ፍርድ ቤትን እንደ ፖለቲካ መሳርያ**

በመንግስተ የፖለቲካ ውሳኔ መሰረት በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ታፍሰው ወደ ቀድሞዎቹ የጦር ማሰልጠኛ ማእከላት መጋዛቸውን ተከትሎ ዳኞችም ወደ ማእከላቱ ከተው አስችሉ መባላቸው ያስታውሷል፡፡

ኮሚሽኑ ሲቋቋም ተጠያቂው ማን እንደሆነ ማጣራት ከኮሚሽኑ ተልእኮ ውጪ እንዲሆን መደረጉ እና ለዚህ ጥያቄ ከገለልተኛ ወገን መልስ ባልተገኘበት ሁኔታ የቅንጅት መሪዎች ታስረው ከመደበኛው ማስቻያ ስፍራ ውጪ ትሎት ተቋቁሞ እንዲያስችል ተደርጓል፡፡

እንከን የለሽ ምርጫ እናከሄዳለን እና ኑ በአቋም ዙርያ እንከራከር ብሎ የመገናኛ ብዙሃንን ክፍት አድርጎ የጋበዘው ኢህአዴግ፤ ከእርሱ ጋራ ሲከራከሩ በፖለቲካ መከራከርያነት ያቀረቡዋቸውን ሃሳቦች ወስዶ ፍርድ ቤት ዘንድ በማቅረብ እነዚያ ተጋብዘው የተከራከሩትን ፖለቲከኞች ወንጀለኞች ለማሰኘት በማስረጃነት ማቅረብ ድረስ ነው የሄደው፡፡

ደም ባፋሰሰው ውዝግብ ላይ ማን ምን ድርሻ ነበረው የሚለው በገለልተኛ አጣሪ አካል ባልተጣራበት ሁኔታ እኔ በግል ጥፋቱ የኢህአዴግ ወይ የተቃዋሚዎች ብቻ ነው ለማለት አልችልም፡ ፡ ይህም ሆኖ የፀጥታ ሃይሎችን አዘጋጅቻለሁ ኮማንድ ፖስትም አዘጋጅቻለሁ በሚል አጀብ ስብሰባ እና ሰልፍን የከለከለው እና የሃይል እርምጃ መውሰዱን ያልካደው ወገን ነጻ ሆኖ፤ ይባስ ብሎም እርሱ ራሱ ከሳሽ ሆኖ ሌላውን ወገን ወንጀል ሰርተሃል ብሎ ማሰሩ እና ተከሳሽ ሆነሃል ብሎ ፍርድ ቤት ማቆሙ ኢህአዴግ ሕግን እና ዳኝነትን በጦር መሳርያነት መጠቀሙን ብቻ ነው የሚያሳየው፡፡

### ሰ) ሽምግልናው በፍርድ ሂደቱ ጣልቃ መግባቱ

በፕሮፌሰር ይስሃቅ ኤፍሬም የተመራው ሽምግልና በሂደቱ ውስጥ ጣልቃ የገባው የቃሊቲው ፍርድ ቤት ፍርዱን ከመስጠቱ ከወራት በፊት ነው፡፡ ሽምግልናው በፍርድ ሂደቱ መሃከል ጣልቃ እንዲገባ ኢህአዴግ መፍቀዱ የሚያመለክተው ጉዳዩ የፖለቲካዊ መሆኑን እንዳልሳተው፤ የፍርድ ሂደቱ እንደ አንድ አማራጭ የፖለቲካ ስልት እንጂ እንደ ብቸኛ እና የመጨረሻው ስልት እንዳልወሰደው ነው፡፡

የፍርድ ሂደቱ መጨረሻ ደረጃው ላይ ሳይደርስ እና ይቅርታ የሚጠየቅበት ደረጃ ላይ ሳይደርስ በፊት ታሳሪዎቹ የይቅርታ ጥያቄ የማቅረባቸው እውነታም ከዚህ የተያያዘ ነው፡፡

እውነታው ይህ መሆኑ እየታወቀ ታሳሪዎቹ በአገሪቱ የይቅርታ ሕግ መሰረት እና በእርሱ መሰረት ብቻ ነው የተፈቱት፤ የሽማግሌዎቹ ሚና ይህንን ከማሳለጥ ያለፈ ፋይዳ አልነበረውም መባሉ ሁኔታውን በቅርብ ይከታተል ለነበረው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሊያሳምን የሚችል መከራከርያ አይወጣውም፡፡ የአንድነት ለፍትህ እና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀ መንበር የወይዘሪት ብርቱካን ሚዴቅሳ ዳግም መታሰር በምክንያትነት እንዲያገለግል ተብሎ ይህ መከራከርያ መቅረቡ ቀደም ብሎ የተወሰነውን እና ታሳሪዎቹን ለመፍታት የተወሰደውን በጎ እርመጃ ያስገኘውን በጎ መንፈስ እና ተስፋ ያንኳስስ እንደሆነ እንጂ የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም፡፡

### ረ) ምርጫ 97፣ ሕገ መንግስታዊነት እና ዴሞክራሲ

ወጤቱ ገና ባልታወቀ ምርጫ መካከል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሕገ መንግስቱ ከተደነገገው ስልጣኑ ውጪ ግንቦት 7 ማታ ይፋ ባደረገው እርምጃ ሕገ መንግስታዊነት እና ዴሞክራሲ አብረው ተደፍቀዋል፡፡

በምርጫ ክርክር ወቅት የቀረበን የሃሳብ ልዩነት ወንጀል አድርጎ፤ እስር ቤት አጠገብ ማስቻያ አቋቁሞ፤ ተፎካካሪዎቹን ተከሳችኋል እና ኑ ተከራከሩ ማለቱ ኢህአዴግ በፖለቲካ መድረክ እና በችሎት መሃከል ያለውን ልዩነት፣ በፖለቲካ መድረክ የሚደረገው ክርክር እና በችሎት ውስጥ የሚደረገው ክርክር ያላቸውን ድንበር ጨርሶ አጥፍቶታል፡፡ በዚሁ ሁኔታ ቁልቁል አፉ የተደፋው የዜጎች ነፃነት ብቻ ሳይሆን የዳኝነት ነፃነት እና ክብርም ጨምር ነው፡፡ ይህ አውነታ በራሱ በዳኝነት ነፃነት እና በዜጎች ነፃነት መካከል ያለው ቁርኝት ባህርያዊ መሆኑን የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡

የስልጣን ክፍፍል፣ ሕገ መንግስት፣ ዴሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብት፣ ምርጫ፣ ዳኝነት፣ አጣሪ ኮሚሽን፣ ሽምግልና ወዘተ የሚባሉት ነገሮች ለኢህዴግ አመባገነናዊ አገዛዝ ሽፋን ሰጪ መፈክሮች መሆናቸው በምርጫ 97 ታይቷል፡፡ ዴሞክራሲ እና ሕገ መንግስታዊነትን አሽቀንጥሮ ልማት እና

ሰላም አመጣለሁ የሚለን ኢህዴግ ምርጫ 97ን ተከትሎ ያፈሰውን ምርት ሊያሳየን አልቻለም፡፡ የምርጫ 97ን ፖለቲካዊ ሙቀት ለማቀዝቀዝ ተብሎ የተረጨው ገንዘብ ይብሱኑ ኢኮኖምያችንን ምስቅልቅል ውስጥ ማስገባቱ፤ ሶስተኛው ዓመቱን የያዘው ምስቅልቅል አለምአቀፉ ቀውስ ተጨምሮበት ነገሮች ከድጡ ወደ ማጡ እንደሆነ ኢህአዴግ ራሱም የሚክደው አይሆንም፡፡ የመሬቱ፣ የወርቁ፣ በጠቅላላው የአገሪቱ ሃብት ዝርፍያ ኮሮጆ መገልበጥ እና ካዝና መዝረፍ ተነጣጣለው የማይታዩ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፆች መሆናቸው በግልፅ አይተናል፡፡

ምርጫ 97 ተከትሎ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ምን ያህል እንደተበላሸ አብሮ እና ተማምኖ ለመኖር እና ለመመካከር ምን ያህል እንቅፋት እንደሆነ እያየን ነው፡፡ የሶማልያው ጉዳይ፣ የእምነቶች ጉዳይ ባንከፍተው ይሻላል፡፡ ከሕገ መንግስታዊነት እና ከዴሞክራሲ መስመሮች መወጣት ምን ያህል አደጋ እንዳለው፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ለሃገራችን ምን ያህል ትልቅ አደጋ እንደሆነም በበቂ ተገንዝበናል፡፡

## ዳግም ትግል ዳግም እስር

የቅንጅት መሪዎች ከእስር ሲፈቱ ደጋፊዎቻቸው ከፖለቲከኞቹ የጠበቁት ሌላ የሆነው ደግሞ ሌላ አንደሆነ ይታወቃል፡፡ መሪዎቹ ለሦስት ተከፈሉ፣ ምልክታቸው እና ስማቸውም እንደዚሁ ተከፋፍለው ታደሉ፡፡ ወይዘሪት ብርቱካን ሚዲቅሳን ጨምሮ በርከት ያሉ የቀድሞው ቅንጅት አመራር አባላትን ያቀፈው አንድነት ለፍትሕ እና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ወደ መድረክ ብቅ ያለውም ከዚህ በኋላ ነበር፡፡

የኢህአዴግ መንግስት ቅንጅትን በማፍረስ ረገድ ትልቅ ድርሻ እንደነበረው ሁሉ የቅንጅት ውስጣዊ ምንነትም በራሱ ለድርጅቱ መፍረስ ትልቅ ድርሻ እንዳለው ከፍቺ በኋላ የተከሰተው ሁኔታ በራሱ ምስክር ነው፡፡ አንድነት ወደ ፖለቲካዊ መድረኩ ሲመጣ የቅንጅትን ድክመቶች አራግፎ በጎ ገጽታዎቹን አጉልቶ ይወጣል በለው የሚጠብቁ እኔን ጨምሮ በርካታ ዜጎች ነበሩ፡፡ በፓርቲው ፕሮግራም በኩል ከታዩት የመሻሻል ምልክቶች ባሻገር የወይዘሪት ብርቱካን የፓርቲው ሊቀ መንበር ሆኖ ወደ መድረኩ መመለስ በራሱ የአንድ በጎ እድገት እና ተስፋ መገለጫ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ይህ ፖለቲካዊ ክስተት ለሌሎቻችን የበጎ እድገት ተስፋ የመሆኑን ያክል በተፃራሪው ለኢህአዴግ ስጋትን ያጫረ ቀይ መብራት ሳይሆን አልቀረም፡፡ የኅዳር 27 ቀን 2001 ዓ.ም የአዲስ አበባው ሕዝባዊ ስብሰባ በተካሄደ በጥቂት ቀናት ውስጥ ተመልሳ ለዳግም እስር መዳረጓ ከዚህ በፊትም እንደገለፅኩት ከዚህ ስጋት የተያያዘ ነው፡፡

ኢህአዴግ ከግንቦት ስምንት ጀምሮ የወሰዳቸው እርምጃዎች አስቀድሞ የተዘጋጀባቸው እንደሆኑ፤ ተቃዋሚዎች ግን በ‹‹ይሆናል›› ያዘጋጁት ዕቅድ ሳይኖራቸው በመቆየታቸው ኢህአዴግ ለወሰዳቸው እርምጃዎች እንኳን በቅጡ ለመመለስ እንደተቸገሩ ከፍ ብየ ጠቁሜአለሁ፡፡ ኢህአዴግ በአሁኑ ወቅት ይዞት ያለው ስልት ከዚያን ወቅት ስልቱ ለየት የሚያደርገው የ97ቱ ‹‹ማዕበል›› እስኪፈጠር ድረስ የማይጠብቅ መሆኑ ነው፡፡ ጠብቆ ‹‹ማዕበሉ›› ጋር ከመጋፈጥ ይልቅ አሁን ይዞት ያለው ስልት ድርጅቶች ተጠናክረው ትልቅ የሕዝብ ድጋፍ እና ሃይል ከማሰባሰባቸው በፊት አስቀድሞ በመምታት ተወዳድሮ የማሸነፍ እቅዳቸውን ማኮላሸት ነው፡፡ በአንድ ዓመት ውስጥ በተከታታይ የወጡት ፓርቲ፣ ፕሬስ፣ መያዶችንና ሲቢክ ማሕበረሰብን የሚመለከቱት ሕጎች፤ ተረቆ ለመጽደቅ ተራውን እየጠበቀ ነው የተባለለትን የፀረ ሽብርተኝነት ሕግ፤ ከዚሁ አስቀድሞ መምታት እና ማኮላሸት የኢህአዴግ ስልት ተነጥለው የሚታዩ እርምጃዎች አይደሉም፡፡

ተቃዋሚዎች ይህንን የኢህአዴግ ስልት ማክሸፍ ካልቻሉ መጠናከሩ እና ሕዝብን ማሰባሰቡ ጋር ሊደርሱ አይችሉም፡፡ እርምጃው በኦፌዴን ዋና ጸሓፊ ተጀመረ ብዙም ሳይቆይ የወይዘሪት ብርቱካን መጣ፡፡ ይህም ሆኖ ጉዳዩ የኦፌዴን ወይም የአንድነት ብለን ገነጣጥለን ልናየው አይገባም፡፡ ጉዳዩን የመላ ኢትዮጵያውያን ጉዳይ፣ ችግሩ የሁላችንም የዚህች አገር ዜጎች ችግር አድርገን መውሰድ፤ ሸክሙን በጋራ መሸከም እንዳለብን መሳት ከቶ አይገባንም፡፡ በተለያየ ድርጅት ልንታቀፍ፣ የተለያዩ ድርጅቶች ደጋፊዎች ልንሆን እንችላለን፤ ለአገራችን ችግሮች መፍትሄ በምንላቸው ፓሊሲዎች ላይ ልዩነት ሊኖረን ይችላል፤ በማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚፈጸመው በደል ግን በራሳችን እንደተፈጸመ

በመቁጠር በጋራ መቆም አለብን። የጋራችን ለሆኑት እሴቶች በጋራ መቆም አለብን። ይህንን የአስተሳሰብ ዳገት መውጣት ካልቻልን በኢትዮጵያ ለውጥ እናመጣለን ማለት የማይታሰብ ነው።

ይህንን የኢህአዴግ ስልት ማክሸፍ የምንችለው በተባበረ ትግል ካልሆነ በተናጠል የትም መድረስ እንደማንችል መገንዘብ ይኖርብናል። የተባበረ መልስ ሲባል ደግሞ የታቀደ እየተደመረ የሚያድግ እንጂ እንዲሁ የቁጭት እና የጥላቻ መሆን የለበትም፤ ካልሆነ ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል እንደሚባለው ሆኖ ብዙም ሳይሄዱ እንደገና ቁጭ ሊያስከትል ይችላል። ይህንን ለማሳካት በምናደርገው ትግል በርካታ እንቅፋቶች ሊጋረጡብን ይችላሉ፤ የሚወስድብን ጊዜ ረጅም ሊሆን ይችላል፤ ፈተናዎችን እና ችግሮችን ተቋቁሞ መዝለቅ ታሪኩ ከሆነ ሕዝብ የመጣን ሰዎች መሆናችንን ግን ከቶ መርሳት የለብንም።

ወ/ሪት ብርቱካን ‹‹ ስዊድን አገር በደረግሽው ንግግር ይቅርታ አልጠየቅኩም ብለሻል›› ተብሎ ለቀረበላት ጥያቄ ሕግን እና የነበረውን እውነታ ተንተርሳ መልሷን ‹‹ቃሌ›› ብላ በሰጠችው የጽሁፍ መግለጫ ይፋ አድርጋለች። ሕግን ተንተርሳ ለሰጠችው መልስ ፍቺ መስጠቱን ለሕግ ተርጓሚ በመተው ፋንታ፣ ራሳቸው ከሳሽ ራሳቸው ሕግ ተርጓሚ ሆነው መልሰው አስሯታል። ይህን ድርጊታቸውንም የሕግ በላይነትን ማስከበር ነው በለውታል።

በኢህአዴግ ቤት የሚፈለገው አንድን ተቃዋሚ ይታሰር የሚለውን የፖለቲካዊ ውሳኔ ላይ መድረስ ነው። የውሳኔው ሕጋዊነት ኢህአዴግን የሚያሳስበው አይደለም። አንድን ነገር ወንጀል ነው ብሎ መደንገግ ለኢህአዴግ ቢበዛ የሃያ አራት ሰዓት ስራ እንደመሆኑ ለውሳኔው ሕጋዊ ሽፋን መፍጠር ችግር አይሆንበትም። በረቂቅ ደረጃ ያለውን የፀረ- ሽብርተኝነት ሕግ ሲፀድቅ ደግሞ ሁሉን ነገር ይሸፍንለታል። ለዚህ መድሃኒቱ  አንድ ሕግ ወጣ አንድ እርምጃ ተወሰደ ብሎ መደናገጥና እርምጃን መቀልበስ ሳይሆን እየታሰሩም ቢሆን ያንን ኢህአዴግ ሊያስቀር የፈለገውን ሕዝባዊ ‹‹ማዕበል›› እንዳይቀርለት ማድረግ ነው። ሕግን ማክበር እና ለሰላማዊ ትግል በፅናት መቆም ይገባል፣ ለሰላማዊ ትግል መቆም ማለት ፍርሃት ማለት እንዳልሆነ ማሳየትም ይገባል።

አመሰግናለሁ

መጋቢት 20 ቀን 2001 ዓ.ም

❶ M.v. Pylee, Select Consitutions of the World Universal Law Publishing Co. P12

❷ Fareed Zakaria, The Future of Freedom W.W. Norton and Company P101-102

❸ George B.N. Ayittey, Africa in Chaos St. Martin's Griffin P311

❹ Fareed Zakaria, Ibid p113-118